| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ግጥም ፤ "ከመቃብር ፡ በላይ" ፡ ዐምድ ። |
| ርእስ ፤ | "አባቴስ ፡ መቼ ፡ ወልዶኝ ፤ እኔስ ፡ መቼ ፡ ተወለድ'ኹ ፤ ለከሓድያን ፡ ጣዖት ፡ ለምስል ፡ እየሰገድ'ኹ ∴ " |
| ደራሲ ፤ | መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ ። (†) |
| ዕለት ፤ | 1970 ዎቹ ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልታተመ ። ) |

# ከመቃብር ፡ በላይ ።

"አባቴስ ፡ መቼ ፡ ወልዶኝ ፤ እኔስ ፡ መቼ ፡ ተወለድ'ኹ ፤

ለከሓድያን ፡ ጣዖት ፡ ለምስል ፡ እየሰገድ'ኹ ∴ "

መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ [1] ።

---

ቅም ፡ አያቴ ፡ አልሰሙ ፥ አለቃ ፡ መብረቁ ፤
ቅድም ፡ አያቴ ፡ አልሰሙ ፥ ተክለ ፡ አብ ፡ ትላቁ ።
ወንድ ፡ አያቴ ፡ አልሰሙ ፥ ናቃቸው ፡ ጨፍቄ ፤
ጥዩፉ ፡ አያቴ ፥ ሸሸጉ ፡ ፈንጥቄ ።
ኵሩዋ ፡ አያቴ ፥ ወይዘሮ ፡ ጥዱ ፡ ነሽ ።
እናቴ ፡ አልሰማችው ፥ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ዙሪያሽ ፤
አባቴም ፡ አልሰማው ፥ ግራዝማች ፡ ወንድ ፡ አፍራሽ ።
ዠግናው ፡ ፈረሰኛ ፥ አጎቴ ፡ ለውሴ ፤
ዐዳኙ ፡ ጦረኛ ፥ ፊታውራሪ ፡ ጣሴ ።
የእንርሱም ፡ አበ ፡ ነፍስ ፥ ውሂበ ፡ ሥላሴ ።
ማን ፡ እንዳንቺ ፡ አክሥቴ ፥ ያብጣቸው ፡ እናት ፤
ያባቴ ፡ ትላቅ ፡ እት ፥ እመት ፡ የትናየት ።
መሪ ፡ ጌታ ፡ ሲሹ ፥ የቀለም ፡ አባቴ ፤
ያባቴ ፡ ባልደረብ ፥ አያል ፡ ሰው ፡ ግምቴ ።
ዐምሳ ፡ እግር ፡ ነ'ኽ ፡ ብሎኝ ፥ ቅምቡርስ ፡ ነ'ኽ ፡ ጭራሽ ፤
ዕቃ ፡ ቅራቅምቦ ፥ ትላትል ፡ ተልከስካሽ ።
ከዚያም ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፥ የዝንጀሮ ፡ ግልገል ፤
ስትፏድድ ፥ ስትዳክር ፡ አረ'ኽና ፡ ገደል ፤
ዥራት'ኽን ፡ ቀስረ'ኽ ፡ በየጥሻው ፡ ስትሮጥ ፤
ስትድ'ኽ ፥ ስትንፏቀቅ ፥ ኧላ'ኽ ፡ እስቲመለጥ ።
ዋል ፥ ዐደር ፡ አለና ፡ ዥራት'ኽ ፡ ሠረገ ፤
በ'ኹለት ፡ እግር'ኽ ፡ ቆም'ኽ ፤ መላጣ'ኽ ፡ ጠገገ ።
ሰውነት ፡ አበጀ'ኽ ፤ መልክ'ኽም ፡ ወረቃ ፤
ግስንግስ ፣ ግማግም ፡ ነበርክ ፡ እኮ ፡ ዕቃ ።
እግዜር ፡ ጨዋታ ፡ ነው ፤ መድ'ኀኔ ፡ ዓለም ፡ የለም ፤
ሰማይና ፡ መሬት ፡ በርሱ ፡ አልተፈጠረም ።
ስግደትና ፡ ጸሎት ፥ ሃይማኖት ፡ ልማድ ፡ ነው ፤
ታቦትና ፡ ሕጉ ፥ መጣፉም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤
ፈጣሪያችን ፡ ማርክስ ፥ ኤንገልስ ፡ ሸሪካቸው ፤
መንፈስ ፡ ቍስ ፡ አካል ፥ ሌኒን ፡ ነው ፡ ልጃቸው ።
ስንክሳር ፡ ግንዘቱ ፤
ገድል ፣ ታምራቱ ፤
ድጓና ፡ ዳዊቱ ።
አንቀጸ ፡ ንስሓ ፣ መጽሐፈ ፡ ቄድር ፤
ይህና ፡ ሌላውም ፡ ያድኃሪ ፡ ነውር ።
ሃይማኖተ ፡ አበው ፣ ሕገ ፡ ምንኵስና ፤
ገዳምና ፡ ደብር ፣ ሱባዔ ፣ ቀኖና ፤
መስቀልና ፡ ገና ፣ ዘመን ፡ መለወጫ ፤
የበዝባዦች ፡ ወግ ፡ ነው ፥ ዋና ፡ መመጥመጫ ።
ሕማማት ፣ ፋሲካ ፥ ፍልሰታና ፡ ጥምቀት ፥
ርኩስ ፣ ውጉዝ ፡ ናቸው ፡ በደርጉ ፡ ሃይማኖት ።
ቤተክሲያን ፣ ቅዳሴ ፣ ምሕላና ፡ ጸሎት ፤
ጾምና ፡ አክፍለት ፥ ቍርባንና ፡ ስግደት ፤
መታለል ፡ ነው ፡ ወዲያ ፥ በዐጕል ፡ መሞኘት ።
ሚስት'ኽም ፡ የወል ፡ ናት ፤ ጋብቻ ፡ በደል ፡ ነው ፤
የእንግዴሁ ፡ ልጅ'ኽ ፡ አባቱ ፡ ኹሉም ፡ ነው ።
ብለው ፡ ሲያናፉብኝ ፥ እምነቴን ፡ ሲያረክሱት ፤
ሃይማኖቴን ፡ ሸረው ፥ መቅደሴን ፡ ሲዘጉት ፤
ባህሌን ፡ አነውረው ፥ ፍቀው ፡ ሲወግዱት ፤
አምላኬን ፡ በይፋ ፡ ሲነቅፉ ፥ ሲሰድቡት ፤
ደምና ፡ ሥጋውን ፡ እሜዳ ፡ ሲደፉት ፤
ቄራቢን ፡ አዋርደው ፡ ቍርባኑን ፡ ሲያወግዙት ፤
የፍልሰታን ፡ በዓል ፡ በዐዋጅ ፡ ሲሽሩት ፤
የማዕዶቱንም ፡ ደርበው ፡ ሲያግዱት ፤
ሰውነቴ ፡ ረክሶ ፥ ዝንጀሮ ፡ ብለውኝ ፤
መታሰቢያ ፡ ፈርሶ ፥ ታሪክ ፡ ተሸሮብኝ ።
አገሬስ ፡ መቼ ፡ ዐውቃኝ ፤ እኔስ ፡ መቼ ፡ ለሷ ፡ ኾንኩ ፤
አምላኬስ ፡ መቼ ፡ ታርቆኝ ፥ እኔስ ፡ መቼ ፡ ተቀደስኩ ።
ለጎግ ፡ ማንጎጉ ፡ ደርግ ፡ ግብር ፡ እየከፈል'ኹ ፥
የርጉማን ፡ ተገዢ ፥ ለነርሱ ፡ እየታዘዝኩ ።
ሚስቴ ፡ ሚስት ፡ አል'ኾነች ፥ እኔም ፡ ባል ፡ አል'ኾንኳት ፤
ልጆቼ ፡ የኔ ፡ አል'ኾኑ ፥ እኔም ፡ የነሱ ፡ አባት ።
አባቴስ ፡ መቼ ፡ ወልዶኝ ፥ እኔስ ፡ መቼ ፡ ተወለድ'ኹ ፤
ለከሓድያን ፡ ጣዖት ፡ ለምስል ፡ እየሰገድ'ኹ ∴

---

1 በ 1970 ዎቹ ፡ በሱዳን ፡ በረሓ ፡ በጠላት ፡ የተገደለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።